# ሐዋርያት ሥራ 1-12 (7)

## ለሐዋርያት ሥራ ቅድመ ዝግጅት

የሃዋርያት ሥራን ስናጠና ብናውቃቸው ጥናቱን የበለጠ እንድንረዳው የሚረዱን ሃሳቦች ስላሉ እነርሱን አጠር አድርገን መመልከት እንሞክራለን።

ይህንን መልዕክት እና የሉቃስን ወንጌል የጻፈው አንድ ሰው እንደሆነና ይህም ሰው ዶክተር ሉቃስ እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም መረጃ ሉቃስ 1፥1 እና ሐዋ ሥራ 1፥1 መመልከት ይቻላል። በእነዚህ ክፍሎች እንደሚታየው ሁለቱንም ሲጽፍ ለአንድ ሰው ማለትም ቴዎፍሎስ በመባል ለሚታወቅ ሰው እንደሆነ እንረዳለን። ሉቃስ 24፥49-53 ትን ማንበብ ሁለቱ መጽሐፍት እንዴት እንደሚያያዙ ጥሩ ሃሳብ ይሰጠናል።

ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1-7 ድረስ ያለው ወንጌል በኢየሩሳሌም እንዴት እንደተስፋፋ ያሳያል። ከምዕራፍ 8-12 ድረስ ደግሞ ወንጌል በሰማርያ እንዴት እንደደረሰና እንደሰፋ ሲያሳይ ከምዕራፍ 13-28 ያለው ደግሞ ወንጌል ለዓለም ሁሉ የደረሰበትን መንገድ ያሳየናል።

ይህ መጽሐፍ የጥንቷን ቤ/ክ አሰራር፥ የነበራቸውን ህብረት፥ ለወንጌል ያሳዩትን ትጋት፥ የጸሎት ህይወታቸውንና ጠቅላላ አሰራራቸውን ስለሚያሳየን የእነርሱ ምሳሌነት የእኛን አገልግሎት ለመመዘንና በአገልግሎታችን ፍሬአማ ለመሆን ስለሚረዳን በጥንቃቄ ማጥናት ይረዳናል።

የሐዋርያት ሥራ የቤተክርስትያን ዋነኛ ተልዕኮ የወንጌል ስርጭት መሆን እንዳለበት ሲያሳየን በተጨማሪም ደግሞ የወንጌል ሥራ ያለመንፈስ ቅዱስ ሃይል ሊሰራ እንደማይችል ግልጽ በሆነ መንገድ ይጠቁመናል።

አማኞች አይሁድም ሆኑ አህዛብ አንድ ህብረተሰብና ቤተሰብ መሆናቸውንም ይህ መጽሃፍ ግልድ የሚያደርግ ሲሆን በዚህም ዘመን ይህንን እውነት የምታስተጋባ ቤተክርስትያን ስለምታስፈልግ ሁላችንም ለዚህ እውነት አስተዋጽዖ ልናደርግ ይገባናል።

በዚህ ጥናት እግዚብሄር በመንፈስ ቅዱስ አማካንነት የግለሰቦችን ህይወት በመለወጥና በመንካት ቤተክርስትያንን እንደሚገለባብጥ በማመን በጸሎት መንፈስ ጥናቱን መጀመር ይኖርብናል። ጌታ ጥናታችንን ፍሬአማ ያድርግልን። አሜን!

# ጥናት አንድ፥ (ሐዋ ሥራ 1፥1-26)

የጥናቱ ዓላማ፥ ቤተክርስትያን በምድር ላይ ያለችበትን ዋነኛ ዓላማ እንድንረዳና ሥራዋን ለማከናወንም የመንፈስ ቅዱስ ሃይል እንደሚስጣት ተስፋ እንደተገባላት ለመመልከት።የጥናት መክፈቻ፥ ቤተክርስትያን ዋነኛውን ትልዕኮዋን የሳተች ሆኖ ተሰምቶህ ያውቃል ወይ?

1. ሐዋርያት ሥራ 1፥1-26 በአንድነት ይነበብ። በቁጥር 1-11 መሰረት ጸሐፊው ሉቃስ ስለኢየሱስ የመጨረሻ ቀናቱ ለቴዎፍሎስ የሚነግረው ምንድነው?
2. ራስሕን በደቀመዛሙርቱ ጫማ ውስጥ አስገብተህ ብትመለከትና በቁጥር 8 ላይ ያለውን ሃላፊነት ለመቀበል የመጀመርያው ብትሆን የሚሰማህን ስሜት ግለጽ።
3. በዚህ ክፍል መሠረት ኢየሱስ ለሰጠው ለአለም ሁሉ ወንጌልን የማድረስ አገልግሎት ብቁ የሚያደርገን ምንድነው?
4. በኢየሱስ ከመካከላቸው መለየት ላስከተለባቸው ተስፋ የመቁረጥና የብቸኝነት ስሜት በቁጥር 10-11 በመላዕክቱ የተነገረው መልክት ስሜታቸውን በምን መንገድ እንደሚቀይረው ትገምታለህ?.
5. ደቀመዛሙርቱ ከመላዕክቱ መልዕክት ከሰሙ በኋላ ያደረጉት ነገር ምን ነበረ?
6. ለራሳቸውም ሆነ ለተልኮአቸው የደቀመዛሙርቱ በአንድነት ሳይለያዩ አብሮ መቆየታቸው አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድነው ትላለህ? ለእኛስ ይህ ድርጊታቸው ምን ያስተምረናል?
7. ጴጥሮስ ተነስቶ ንግግር ሲያደርግ የራሱን ሃሳብ ሳይሆን በቀጥታ ወደ እግዚአብሄር ቃል እንደመለሳቸው እንመለከታለን። በምርጫው ለወሰዱት እርመጃ በቃሉ ላይ መቆማቸው ምን ያህል የልብ ድፍረት ይሰጣቸዋል?
8. ለወንጌል ስርጭት መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋራ እንዳለ ማወቅህ የሚያመጣው ልዩነት ምንድነው? ዛሬም ብቻህን የምትወጣ ስላልሆነ በልበሙሉነት አገልግሎትህን መፈጸም ትጋ።

# ጥናት ሁለት፡ (ሐዋ ሥራ 2፥1-47)

የጥናቱ ዓላማ፡ የመንፈስ ቅዱስን ሐይል በትክክል ለመረዳትና የወንጌል ምስክርነት አገልግሎት ያለርሱ ሊሰራ እንደማይቻል ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡ መንፈስ ቅዱስን ከቤተክርስትያን አውጥተህ ብትመለከት ቤተክርስትያን ምን እንደምትመስል ያለህን ሃሳብህን ግልጽ።

1. ሐዋ ሥራ 2፥1-47 በአንድነት ይነበብ። መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ወቅት አማኞቹ የነበሩበት ሁኔታን ግለጽ።
2. የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በሰሚዎቹና በተመልካቾቹ ላይ ያስከተላቸውን ነገሮች ዘርዝር። (ቁ5-13)
3. ጌታን ሶስት ጊዜ የካድውን ሰው በቁ 14-36 ላይ ስናየው ምን ልዩነት ታይበታለህ? ይህንን ዓይነት ልዩነት በህይወቱ ያመጣው ምንድነው ትላለህ?
4. በቁ 1-4 የተፈጸመው ነገር አስቀድሞ በኢዩኤል ትንቢት ተነግሯል። ይህ ሁኔታ ለእኛ ለምናምን ምንን ያረጋግጥልናል?
5. ቁ 37 ላይ ይህንንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ የተባለው ምን ስለሰሙ ነው የእነዚህ ሰዎች ልብ የተነካው?
6. ቁ 39 ኘን ስታነብ የተናገረው የተስፋው ቃል የሚጠቀልላቸው ዘመናትና ትውልዶች የትኞቹ እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር።
7. ቁ42 ትን ስናነብ በመንፈስ መሞላት ብቻውን በቂ እንዳልሆነና የሚቀጥል ነገር እንዳለ እንገነዘባለን። ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋራ አብረን ማስኬድ ያለብን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
8. ቁ46-47 ያለው ክፍል ደግሞ በመንፈስ የተሞሉ ሰዎች በህይወታቸው ተገልጠ የሚታዩትን ነገሮች አስፈሮልናል። እነዚህን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር።
9. ከዛሬው ጥናት የመንፈስ ቅዱስን ለመንፈሳዊ ህይወትህ አስፈላጊነት ምን ያህል ተረዳህ? ለግልህ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስትያንህም ያለ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሁሉ ድካም መሆኑን በመገንዘብ የዘወትር ጸሎት ርዕስህ አድርገህ ያዘው።

# ጥናት ሶስት፡ (ሐዋ ሥራ 3፥1-26)

የጥናቱ ዓላማ፡ እግዚአብሄር በሰዎች ህይወት ተአምራትን ሲፈጽም አብዛኛውን ጊዜ ለተፈወሰው ሰው ወይም ለሌሎች ወንጌል ማድረሻ ምክንያት እንዲሆን መሆኑን ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡ በአንተ አስተያየት የማያምንን ሰው ለጌታ ልቡን እንዲከፍት ከሚያደርገው ዋነኛው ነገር ምንድነው ትላለህ?

1. ሐዋ ሥራ 3፥1-26 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካሄደውን ሁኔታ በራስህ ቋንቋ በአጭሩ ለወገኖች ተናገረው።
2. ቁ1-3ትን በማንበብ ይህ ለማኝ ስለሚገኝበት ሁኔታ ምን መረዳት እንችላለን?
3. በቁ4-7 መሰረት ጴጥሮስና ዮሐንስ በኪሳቸው አንዲትም ሳንቲም የላቸውም ማለት ነው ወይስ ከአነጋገሩ የምትረዳው ምንድነው? በእኛ ዘመንስ የዚህ ዓይነቱን ተአምር እግዚአብሄር እንዲሰራ ከእኛ ምን ይጠበቃል ትላለህ?
4. የተፈወሰው ሰው ለፈውሱ የሰጠው ምላሽ ምን ነበረ? ተመልካቾቹስ ይህ የሆነው ነገር በህይወታቸው ያስከተለው ነገር ምንድነው? ቁ 8-11ድን ተመልከት።
5. ጴጥሮስ እግዚአብሄር ያደረገውን ተአምር ተልዕኮአቸውን ማከናወኛ መንገድ አድርጎ ተጠቀመ ማለት የሚቻለው እንዴት ነው? ቁ 12-26
6. ቁ12 ላይ "በገዛ ሃይላችን ወይስ እግዚአብሄርን በመፍራታችን..." በቁ 16 ደግሞ "በስሙ በማመን..." የሚሉትን አባባሎች ስታነብ ስለተአምራት አፈጻጸም ምን ትማራለህ?
7. ጴጥሮስ በቁ23 ላይ "ይህን ነብይ የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ከህዝብ ተለይታ ትጥፋ።" በማለት ተመልካቾቹን ከተአምራቱ ወደ ክርስቶስ መጠቆሙ ስለተአምር ምንነት ምን ያስተምረናል?
8. ጌታ ተአምራት ሲሰራ ስታይ የምትደሰትበት ዋነኛ ምክንያት ለምንድነው? ሰዎች የሥጋ መዳንን ሲያገኙ የሚያስደስተን ነገር ቢሆንም፣ ለራሳቸው ወይም ለሌሎች የነፍስ መዳን መንገድ ሆኖ ሲገኝ ግን የበለጠ ደስታን ሊሰጠን ይገባል።

# ጥናት አራት፡ (ሐዋ ሥራ 4፥1-31)

የጥናቱ ዓላማ፡ በአመቺ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ተቃውሞ በበዛበትና በአስቸጋሪ ሁኔታም ውስጥ ከወንድሞቻችን ጋራ በአንድ ልብ አብረን መቆም እንደሚያስፈልገን ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡ እምነትህን ለማስጣል ሰዎች የሞከሩበትን ጊዜ ስታውሳለህ? ምላሽህን ምን ነበረ?

1. የሐዋርያት ሥራ 4፥1-31 በአንድነት ይነበብ። ቁጥር 1-2 ስታነብ የካህናት አለቆች የመቅደስ አዛዡንና ሰዱቃውያንን የተቸገሩበት ነገር ምንድነው ይላል? ሐዋርያቱስ ተሳስተው ያደረጉት ድርጊት ይመስልሃል ወይ?
2. በቁ3-4 መሰረት በሐዋርያቱ ላይ የተወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ሐዋርያቱ አስቀድመው ስለዘሩት ዘር ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?
3. በቁ13-14 መሰረት ህዝቡ ስለ ዮሃንስና ጴጥሮስ የነበራቸው አመለካከት ምን ይመስል ነበረ? አንተስ ከኢየሱስ ጋራ እንዳለህ የሚገልጥህ ነገር አለህ ወይ?
4. የጴጥሮስ ስብከቶች በተለይም 4፥12, 3፥22, 2፥36 ትኩረታቸው ወይም ማዕከላዊ ሃሳባቸው ምን ነበረ? ይህንን ስታይ የአንተም ሆነ የቤተክርስትያን ማዕከላዊ መልዕክት ምን መሆን አለበት ትላለህ?
5. ቁጥር 19-20 ስናነብ ለሐዋርያት የተሰጣቸውን ጥብቅ ማስጠንቀቅያ እናያለን። ዛቻውን ክብደት ስታይ የሐዋርያቱን ምላሽ አስደናቂ የሚያደርገው ለምንድነው?
6. በቁጥር 23-31 ላይ ወገኖች ሁኔታውን ሲነግራቸው ያደረጉት ነገር ምን ነበረ? ጸሎታቸውን በመመልከት ይህ የተፈጸመው በእኛ መሃል ቢሆን እንጸልይ ነበረ ብላችሁ ከምትገምቱት የጸሎት ዓይነት ጋራ በማነጻጸር ተወያዩበት።
7. የአማኞቹ የጸሎት ጥያቂያቸው ዋነኛ ሐሳብ ምን ነበረ? (ቁ29-30)
8. በቁ31 ላይ የሆነውን ነገር በራስህ ቋንቋ ተናገር። በጸሎት፣ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና፣ ቃሉን በግልጥ በመናገር መሃል ያለውን ግንኙነት አስረዳ።
9. ቁ24 በማንበብ በአንድ ልብ መቆማቸው ምን ያህል ጥቅም ነበረው? አንተስ ከሌሎች ጋራ በጸሎትና በሚያስፈልገው ሁሉ አብረህ ለመቆም ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት አምስት፡ (ሐዋ ሥራ 4፥32-5፥16)

የጥናቱ ዓላማ፡ የአማኞችን ማታለልና መሸንገል ብንችለም እንኳን መንፈስ ቅዱስ የልብን ስለሚያይ አንድ ቀን መጋለጥ ሊኖር እንደሚችል እንዳንዘነጋ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡ ከሌሎች ወንድሞችና እህቶች ጋራ አንድ ልብ እንዳለህ ይሰማሃል ወይ? ካልሆነስ ለምን ይመስልሃል?

1. የሐዋ ሥራ 4፥32-5፥16 በአንድነት ይነበብ። 4፥32-34 ይህ ቁጥር ስለአማኞች የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር። ንብረታቸውን በአንድነት ለማድረግ ያደፋፈራቸው ዋነኛ ነገር ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
2. በ4፥32-37 ላይ በየልብና በሃሳብ አንድ የመሆናቸው መግለጫ አድርገው የተጠቀሙበት ድርጊት ምን ነበረ?
3. 5፥1-2 ስታንብ ሐናንያና ሰጲራ የሌሎቹን ዓይነት ድርጊት ማድረግ የፈለጉበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? የእነርሱን አድራጎት ልዩ የሚያደርገውስ ምንድነው?
4. ጴጥሮስ በቁ4 ላይ ከተናገረው፣ ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥከውስ በኋላ በስልጣንህ አልነበረምን? ከሚለው አባባል ስጦችንን በተመለከተ ምን መረዳት እንችላለን?
5. ቁጥር 11 የሚናገረው በቤተ ክርስትያን ላይ ወደቀ የሚለው ፍርሃት ምን ዓይነት ለውጥ እንደሚያስከትል ትገምታለህ? የዚህ ዓይነቱ ፍርሃት ለቤተክርስትያንህ የምትመኘው ዓይነት ፍርሃት ነው ወይ? ለምን?
6. ሌሎቹ አማኞች ያደረጉትን ድርጊት ሃናንያና በሰጲራ ካደረጉት ጋራ በማነጻጸር ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው? በዚህ ዘመን የክርስቶስን አካል የመንዋሸባቸው መንገዶች እንዳሉ በምሳሌ አስረዳ።
7. በወገኖች መሃል መንፈሳዊ መስለህ ለመታየት ሞክረህ ታውቃለህ ወይ? በመምሰልና ብማሰመሰል መኖር አንድ ቀን መጋለጥ ሰላለ የሆንከውን ሆኖ መኖር ጌታ ያከብራል። 4፡4ትን ተመልከት።

# ጥናት ስድስት፥ (ሐዋ ሥራ 5፥17-6፥7)

የጥናቱ ዓላማ፥ የሲያል ደጆች አይችሉአትም የተባለላት ቃልኪዳን እውነት እንደሆነ ለማየትና ባሳደዱአት መጠን ደግሞ ቤተክርስትያን እንደምታድግ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፥ ስለወንጌል በህይወትህ ስደት ከቤተሰብም ሆነ ከሌላ አቅጣጫ ገጥሞህ ያውቃል ወይ? እንዴት ተወጣኸው?

1. ሐዋ ሥራ 5፥17-6፥7 በአንድነት ይነበብ በቁ17-20 የሆነው ነገር ምን ነበረ?
2. በ5፥28 ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁሞቆታችኋታል። የሚለው ሃሳብ በሃዋርያት እየተካሄደ ስላለው የወንጌል ስርጭት ምን ይነግረናል?
3. 5፥29 ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሄር ልንታዘዝ ይገባናል። የሚለውን አባባል በ4፥19 ላይም እናየዋለን። የዚህ ዓይነቱን ተደጋጋሚ መልስ መስጠታቸው ስለነዚ ሰዎች የሚነግረን ነገር ምንድነው?
4. 2፥32, 3፥15, 5፥32 እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን። ይህንን እውነት ጴጥሮስ እየደጋገመ የሚናገርበት ምክንያቱ ምንድነው?
5. 5፥33-39 በማንበብ የገማልያል ንግግር ስለእግዚአብሄር ሥራ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
6. 5፥41 ስታነብ ሐዋርያቱን ያስደሰተው ነገር ምንድነው ይላል? አንተስ ስለክርስቶስ መከራ ገጥሞህ ያውቃል ወይ? የተሰማህን ስሜት ግለጥ።
7. 6፥1 ስናነብ በመከራው ጊዜ አማኞች እንደበዙና ከዚያም ጋራ አብሮ ችግር እንደመጣ እናያለን። መብዛታቸው ያስከተለው ችግር ምን ነበረ?
8. ለተፈጠረው ችግር ሐዋርያቱ መፍትሄ ይሆናሉ ያሏቸው ምን ዓይነት ሰዎችን ነበረ?
9. ችግሮቹ በበዙ ቁጥር ወንጌልም በዚያው መጠን መስፋቱ ምን ያስተምርሃል? ችግር ለቤተ/ክ ዕድገት ሊውል የሚችል ነገር ስለሆነ በዚያ ዓይነት ልናስተናግደው ይገባናል።

# ጥናት ሰባት፤ (ሐዋ ሥራ 6፥8-7፥60)

የጥናቱ ዓላማ፤ በእስጢፋኖስ ሕይወት የተገለጠውን የመንፈስና የጥበብ ሙላት በመመልከት በኛ ሕይወትም ሊሰራ የሚችልበትን መንገድ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፤ እግዚአብሄርን በውስጡ የምታይበት፥ ጥበብና መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው የምትለው ሰው አለህ ወይ?

1. የሐዋ ሥራ 6፥8-7፥60 በአንድነት ይነበብ። በ6፥8-11 የምናያቸው ሰዎች በእስጢፋኖስ ላይ የተነሱበት እውነተኛው ምክንያት ምን ይመስልሃል?
2. 7፥1-8 ትን ስታነብ እግዚአብሄር ለአብርሃም የተስፋ ቃል እንጂ በጊዜው ስንዝር የምታህል መሬት እንኳን እንዳልሰጠው ይታያል። በምንባቡ መሠረት የተስፋ ቃሉ ቢያንስ ከምን ያህል ዘመን በኋላ እንደሚፈጸም ነው የሚያሳየን?
3. ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃሉ መፈጸምና የጊዜውን መርዘም ስትመለከት ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን ትማራለህ?
4. የዩሴፍ በባርነት መሸጥ(ቁ9)፤ የዩሴፍ ቤተሰብ ሁሉ መራብ(ቁ 11)፤ ሕፃናት ሲወለዱ መገደል(ቁ 19)፤ የአባቶች መጨነቅ(ቁ 19) እና የመሳሰሉት ለተስፋ ቃሉ መፈጸም እንቅፋት የሚመስሉት ነገር ግን ለተስፋ ቃሉ መፈጸሚያ መንገዶች መሆናቸው አንተ ለቃሉ ለሚኖርህ አመለካከት ምን አስተዋጾ አለው?
5. በ7፥25-29 ሁለቱ ወንድማማቾች ሲጣሉ ማድረግ የፈለገውና እነርሱ ደግሞ እርሱን ባዩበት አመለካከት መሃል የነበረውን ልዩነት አስረዳ?
6. ቁ 35 ላይ ሰዎቹ ስለሙሴ በተናገሩትና እግዚአብሄር ሙሴን ምን አድርጎ እንደላከው በምናየው ሃሳብ ምን መመሳሰል ወይ ምን መለያየት ታያለህ?
7. በ7፥1-50 ላይ እስጢፋኖስ የእስራኤልን አመሠራረትና አሁን የደረሱበትን ሁሉ በአንድ ምዕራፍ በቅደም ተከተል ሳያዛንፍ ማስረዳት መቻሉ ስለዚህ ሰው ምን ያስተምርሃል? ለራስህ ህይወትስ ምን ትወስዳለህ?
8. 7፥51-60 የእስጢፋኖስን በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞላ ህይወት እንደሚኖር የሚያስረዱትን ማረጋገጫዎች አሳይ።
9. ሕይወትህ የመንፈስ ቅዱስና የጥበብ ሙላት እንዳለብህ የሚያሳይ ኑሮ መኖር እንድትችሉ የህብረት ጸሎት አድርጉ።

# ጥናት ስምንት፣ (ሐዋ ሥራ 8፥1-40)

**የጥናቱ ዓላማ፣** ብዙዎችን ለመድረስ የሚልከንን ያህል እግዚአብሄር አንዳንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ ሊልከን እንደሚችል በመገንዘብ ለመታዘዝ ልባችንን እንድናዘጋጅ ለመማር።
**የጥናት መክፈቻ፣**

1. የሐዋ ሥራ 8፥1-40 በአንድነት ይነበብ። በ1፥8 በተሰጠው ተልዕኮ መሠረት ወንጌል ወደ ሰማርያ ሲወጣ ይታያል። ለዚህ የወንጌል መስፋት ምክንያት የሆነው ምንድነው ትላለህ?
2. በቁ 6 መሰረት ፊሊጶስ የተናገረውን በሙሉ ልብ ለመቀበል ተጨማሪ ምክንያት የሆናቸው ነገር ምን ነበረ?
3. በ8፥4-13 ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በግልጽ የታየባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር።
4. በቁ 14 ላይ ምንም እንኳን ወንጌል በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ቢሆንም ጴጥሮስና ዮሐንስ በሰሩት ሥራ ውስጥ መጥተው መግባታቸው እነ ፊሊጶስን አልከፋቸውም። ይህ አሰራር ዛሬስ ለእኛ ምን ትምህርት ይሰጠናል?
5. ቁጥር 26 ትንና 40 በማንበብ መንፈስ ቅዱስ በወንጌል ስርጭት ላይ ሊኖረው ስለሚገባው አስተዋጽዖ ምን ያስተምረናል?
6. 8፥26-40 የተከናወነው ነገር የሃዋ ሥራ 1፥8 እስከ ምድር ዳር ለሚለው የወንጌል ትልዕኮ መፈጸም መንደርደሪያ ሊሆን የሚችለው በምን መንገድ ነው?
7. የፊሊጶስን የወንጌል አቀራረብ ዘዴ ለማናቸውም ክርስትያን ጥሩ የምስክርነት መነሻ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ተናገር። ስለ ጥምቀትስ ይህ ክፍል ምን ትማራለህ?
8. ቁ 6 ላይ ለህዝብና በቁ 27 ላይ ደግሞ ለአንድ ግለሰብ ፊሊጶስ ሲላክ እናያለን። ከዚህ አይነቱ የእግዚአብሄር አሰራር ምን እንማራለን?
9. ከዚህ ክፍል ለተሻለ የወንጌል ምስክርነት የሚረዳህ ምን ትምህርት ተማርክ? በምን መንገድስ ልትለማመደው ታስባለህ?

# ጥናት ዘጠኝ (ሐዋ ሥራ 9፥1-31)

**የጥናቱ ዓላማ፤** እያንዳንዳችን በሌላችን ህይወት ውስጥ መልካም አስተዋጽዖ ልናደርግ እንደምንችል በማሳየት ለዚያ አይነቱ ምግባር ለማነሳሳት፡፡

**የጥናት መክፈቻ፤**

1. የሐዋ ሥራ 9፥1-31 በአንድነት ይነበብ። 7፥58-60, 8፥1-3, 9፥1-2 ትን በማንበብ ስለ ጳውሎስ ማንነት ምን ትረዳለህ?
2. 9፥3-9 በጳውሎስና በኢየሱስ መሃል የነበረውን ውይይት በራስህ ቃላት አስረዳ።
3. ቁ 6 "ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?" ጳውሎስ ይህንን ከጠየቀ በኋላ የወሰዳቸው ድርጊቶች በምን ዓይነት የአባባሉን እውነተኛነት ያረጋግጣሉ? ከዚህ አባባሉ የምትማረው ነገር ምንድነው?
4. «...የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል፡፡» ቁ 6 ጌታ ለምንድነው ወደ ሌሎች ያስተላለፈው ለምን ራሱ አልነገረውም?
5. በ9:10-16 በጌታና በሐናንያ መካከል የተካሄደውን ውይይት ተናገር፡፡ እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ለጳውሎስና ለሐናንያ ለሁለቱም መናገሩ ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን ያስተምረናል?
6. ሐናንያ በቁጥር 17 ላይ ጳውሎስን "ወንድሜ" በማለት ሲጠራው እንመለከታለን፡፡ ለምንድነው ይህ አጠራሩ ድንቅ ነገር ሆኖ ሊታየን የሚገባው?
7. የጳውሎስ ጌታን ማመን ወደ ጌታ ሊመጡ አይችሉም ብለን ተስፋ ስለቆረጥንባቸው ሰዎች ምን ያስተምረናል?
8. ቁ 20 "ወዲያው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በምኩራቦች ሰበከ።" ይህ አባባል ምስክርነትን በተመለከተ ምን እውነት ያስተምረናል?
9. በ9:26-30 ከሰፈረው ሃሳብ በመነሳት በርናባስ በጳውሎስ ህይወትና አገልግሎት ውስጥ የነበረው አስተዋጽዖ ምን ነበረ?
10. የሐናንያና የበርናባስ አስተዋጽዖ በጳውሎስ ህይወት የተለያየ እንደሆን እናያለን፡፡ በዚህ አንጻር አንዳችን ለሌላችን ልናደርግ ስለምንችለው ነገር ምን ትማራለህ?

# ጥናት አሥር፣ (ሐዋ ሥራ 9፥32-10፥48)

**የጥናቱ ዓላማ፣** የእግዚአብሄር ቃል እየመረጥን የሚስማማንን ብቻ የምንሰማው ሳይሆን አንድም ነገር ሳናስቀር የምንሰማውና የምንታዘዘው መሆን እንዳለበት ለመማር።

**የጥናት መክፈቻ፣**

1. ሐዋ ሥራ 9፥32-10፥48 ትን በአንድነት ይነበብ። በ9:32-43 ባለው ክፍል የተከናወኑትን ሁለት ተአምራቶች ተናገር። ሁለቱ ተአምራቶች ያስገኙት ውጤት ምን ነበረ?
2. በ10፥1-2 መሰረት ቆርኔሊዮስ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ነው የምናየው?
3. ቆርኔሊዩስ በ10፥1-2 ያሉት ነገሮች ሁሉ ቢኖሩት ይህ ሁሉ በቂ እንዳልሆነና ከጴጥሮስ መስማት የነበረበት መልዕክት እንደነበረ 10፥6, 10፥43, 11፥14 ያሳየናል። ከዚህ የምትማረው ነገር ምንድነው?
4. «እግዚአብሄር አንተን/አንቺን እንዳገባ ተናገረኝ» እና ለመሳስሉት አባባሎች ለሚጠቀሙ ሰዎች ይህ ክፍል ምን ዓይነት መመሪያ ሊሰጥ ይችላል ትላለህ? (ለጴጥሮስም ለቆርኖሊዎስም እግዚአብሄር መናገሩ ማለት ነው)
5. በምን ዓይነት መንገድ ነው እግዚአብሄር ጴጥሮስ ቆርኔሊዩስን እንዲቀበል ያዘጋጀው? 10፥9-33
6. ቆርኔሊዩስ በ10፥24 ላይ ስናየው በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ሁሉ መልካሙን የወንጌል መልዕክት እንዲሰሙ መሰብሰቡ ስለሰውየው የሚነግረን ነገር ምንድነው?
7. ስለ ጴጥሮስ ቁ10፥28-29 በማንበብ አስቀድሞ ስለነበረው አስተሳሰብ ምን ታያለህ? አመለካከቱ ከራዕዩ በኋላ መቀየሩን የሚያመለክተን የትኛው ክፍል ነው?
8. «እንግዲህ አንተ ከእግዚአብሄር ዘንድ የታዘዝከውን ሁሉ እንድንሰማ እኛ ሁላችን አሁን በእግዚአብሄር ፊት በዚህ አለን።»10:33 ከዚህ አባባሉ ስለ ቆርኖሊዎስ ምን ታያለህ? በ10፥44-48 እግዚአብሄር ጥማታቸውን በምን ዓይነት አረካላቸው?
9. «የታዘዝከውን ሁሉ እንድንሰማ» የሚለው አባባሉ እግዚአብሄርን ሰለመስማት ምን ያስተምረናል? አንተስ እግዚአብሄር የሚናገርህን ሁሉ ለመስማት ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት አሥራ አንድ፣ (ሐዋ ሥራ 11፥1-30)

የጥናቱ ዓላማ፣ የወንጌል ስርጭት በግልም ሆነ በቤተ ክርስትያን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር እንደሆነ ለማሳሰብ::

የጥናት መክፈቻ፣

1. ሐዋ ሥራ 11፥1-30 በአንድነት ይነበብ። ቁ 2ትንና ቁ 18ትን በማነፃጸር ስለጠያቂዎቹ ምን ትማራለህ?
2. በቁ 4-18 ላይ ጴጥሮስ ለአህዛብ ወንጌልን በማድረሱ ለደረሰበት ተቃውሞ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ካደረገው ነገርስ አንተ ለሚገጥምህ ተቃውሞ ማድረግ ስላለብህ ነገር ምን ያስተምርሃል?
3. በቁ 15-17 መሠረት የሰዎቹን አመለካከት የቀየረው የትኛው ሃሳብ ነው? ለምን?
4. በቁ 19-20 መሰረት ለወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ የመድረስ ምክንያት የሆነው የትኛው ሰው ነው? እንዴት?
5. ወንጌል ለአህዛብ በትልቅ ፍጥነት በመድረሱ ለእነዚህ አዲስ ላመኑት ሰዎች ቤተ ክርስትያን የወሰደቻቸውን ጥንቃቄዎች ዘርዝር። (ቁ 22-30)
6. የበርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም መላክ ዋናው ምክንያት ምን ነበረ? ውጤቱስ?
7. ቁጥር 25-26 ትን በማንበብ በርናባስ ለምንድነው ጳውሎስን ፍለጋ የሄደው? በርናባስ ያደረገውን ድርጊት በዘመናችን ከሚታየው ሁኔታ ጋራ በማነጻጸር ተናገር::
8. በቁ 29-30 መሰረት በቀድሞ ዘመን አማኞች አንድነታቸውን ይገልፁ ከነበሩባቸው ነገሮች አንዱ ምን ነበረ? አንተስ የሥጋዊ ነገር ከጎደላቸው ጋራ ህብረትህን ለመግለጽ ምን አይነት እርምጃ ትወስዳለህ?
9. ወንጌልን ማሰራጨት በተመለከተ የጥንቷ ቤተክርስትያን ስለምትሰጠው ትኩረት ምን ታያለህ? በራስህ ህይወትም ሆነ በቤተ ክርስትያን የወንጌል ስርጭት ቅድሚያ እንዲሰጠው የምትችለውን ሁሉ አድርግ::

# <u>ጥናት አሥራ ሁለት፣ (ሐዋ ሥራ 12፥1-25)</u>

የጥናቱ ዓላማ፣ የእግዚአብሔር አገልግሎት ያዝ ለቀቅ የሚደረግ ነገር ሳይሆን ከፍጻሜ እስክናደርስ ድረስ በትጋት የምናከናውነው ነገር እንደሆነ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፣

1. ሐዋ ሥራ 12፥1-25 በአንድነት በማንበብ በዚህ ክፍል ተዋናኞቹ እነማን እንደሆኑ ዘርዝር። እያንዳቸው በሁኔታው ውስጥ የነበራቸውን ተሳትፎ ዘርዝር።
2. ቁ 1-5 ትን ስታነብ ሔሮድስ እየወሰደ ያለውን እርምጃ እንዲወስድ የገፋፋው ነገር ምንድነው ትላለህ?
3. በጴጥሮስ መታሰር ቤተክርስትያን የወሰደችው እርምጃ ምን ነበረ?
4. ይህ ቤተክርስትያን የወሰደችው እርምጃ በዚያን ዘመን ስለነበረችው ቤተክርስትያን ምን ይጠቁማል? ይህ ሁኔታ በዘመናችን ቢከሰት በምን መንገድ መፍትሄ የሚፈለግ ይመስልሃል?
5. በቁ 13-16 ላይ እየጸለዩ የነበሩበት ነገር መልስ መምጣትና እነርሱ ደግሞ በቁ 15 ስላሳዩት ሁኔታ ምን ታስባለህ? በአንተስ ህይወት የዚህ ዓይነት ነገር ገጥሞህ ያውቃል ወይ?
6. 9፥23-25 እና 12፥17-19 ጳውሎስና ጴጥሮስ ከሚፈልጓቸው ሰዎች እንዴት እንዳመለጡ ያሳየናል። ከእነዚህ ሰዎች አድራጎት የምትማረው ነገር ምንድነው?
7. ቁ 23-24ትን በማንበብ ትልቅ ይመስል ስለነበረው ስለ ሄሮድስና ትንሽ ይመስል በነበረው ስለ እግዚኣብሄር ቃል የተነገረውን ነገር አነፃጽር። ከዚህ ውስጥ ስለእግዚኣብሄር ቃል ምን ትማራለህ?
8. "በርናባስና ሳውልም አገልግሎታቸውን ፈጽመው.." የሚለው ሐሳብ አገልግሎትን አስመልክቶ ምን ያስተምርሃል? ጀምሮ ከግብ ማድረስ ትልቅ ጸጋ ስለሆነ ከዚህ አንጻር ጌታ እንዲረዳችሁ ሁላችሁም በአንድነት ጸልዩ።

# ሐዋርያት ሥራ 13-28 (7)

## ጥናት አስራ ሶስት (ሐዋ ሥራ 13፡1-52)

**የጥናቱ ዓላማ፡ መከራና ስደት ለአማኝ የማይቀር ቢሆንም እግዚአብሄር ደግሞ የልጆቹን ልብ በደስታ በመሙላት የሚያጽናና መሆኑን ለማስታወስ።**

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ደቀመዛሙርቱም በደስታና በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡››

1. ሐዋ ሥራ 13፥1-52 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። መንፈስ ቅዱስ ለአንፆኪያ ቢተ ክርስትያን ድምፁን ያሰማው ምዕመናኑ በምን ዓይነት ሁኔታ ሳሉ ነበረ?
2. ቁ15-16 ጳውሎስ የተሰጠውን እድል ሳያቅማማ ሲቀበል ይታያል። ይህ ሁኔታ ጳውሎስ የሚነግረን ነገር ምንድነው? ዛሬ እርሱ እንደተጠየቀው ብትጠየቅ ቃል ይኖርሃል ወይ?
3. በቁ26 ላይ ወንጌልን ስላቀረበበት አቀራረቡ ምን ምን ሃሳብ መስጠት ትችላለህ? የወንጌል አቀራረብ በተመለከተ ምን ያስተምረንል?
4. በቁ 38-41 መሠረት የጳውሎስ ማዕከላዊ የወንጌል መልዕክት ምንድነው?
5. የወንጌሉን መልዕክት የሰሙት ሰዎች ለመልዕክቱ የሰጡት የተለያየ ምላሽ ዘርዝር።(ቁ 42-47) ይህንን ስታይ ስዎች ለወንጌል ስለሚሰጡት ምላሽ ምን ማለት እንችላለን።
6. ቁ 49-51 ሰይጣን በወንጌል ላይ ስላለው ጥላቻ ምን ያሳይሃል? ዛሬስ የጠላት አሰራር ከዚህ የተለየ ሆኖ ታየዋለህ ወይ?
7. ቁ 52ትን ስናይ ጠላት በህዝቡ ላይ ላመጣው ስደት የእግዚኣብሄር ምላሽ ምን ነበረ? ልጆቹን በመንፈስ ቅዱስና በደስታ የሞላበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
8. ሰይጣን መከራን ቢያመጣ እግዚ አብሄር ደግሞ በዚያው ውስጥ ሆነን እንድንደሰት ያደርጋል። በምታልፍበት በመከራህ ውስጥ ምን ያህል ደስታን ትለማመዳለህ?

# ጥናት አሥራ አራት፣ (ሐዋ ሥራ 14፥1-28)

የጥናቱ ዓላማ፣ ምንም ዓይነት ታላቅ አገልጋይ ብንሆን ለቤ/ክ ራሳችንን አስገዝተን መኖር አስፈላጊ ነገር መሆኑን ከጳውሎስና ከበርናባስ የህይወት ልምምድ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ከኢጣልያም እስከ አሁን ላከናወኑት ሥራ በእግዚአብሄር ጸጋ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ተመለሱ››

1. ሐዋ ሥራ 14፥1-28 በአንድነት ይነበብ። በ13፥50 እና በ14፥2 ላይ ስለሚገኙት አሳዳጆች ምን ተመሳሳይ ነገር ታያለህ?
2. በቁ 5-7 ላይ አማኞች ወንጌልን ለሌሎች ለማድረስ የተጠቀሙበት ዘዴ ወይም ጥበብ ምን ነበረ? ለምንድነው ይህ ዓይነቱ አሰራር ጥበብ ሆኖ የሚቆጠረው?
3. በቁጥር 8 ላይ የተጠቀሰው ሰው ስላለበት ሁኔታ የተገለጹትን ነገሮች ዘርዝር።
4. በዚህ ሰው ህይወት የተሰራው ተአምራት ምን አስከተለ? ሐዋርያቱስ ለተከተለው ሁኔታ ምላሽ የሰጡት በምን ዓይነት ነበረ? (ቁጥር 8-18)
5. 13፥50, 14፥5, 14፥19 እና የመሳሰሉት ወንጌል ሲሰበክ ጠላት ዝም ብሎ እንደማይቀመጥ ያሳየናል። 14፥20-22 ከዚህ ሁኔታ አንጻር ምን ያስተምረናል?
6. ከላይ ባነበብነው ክፍል(14፥21-22) አገልጋዩች ለምዕመናን የተናገሯችውን ነገሮች ዘርዝር። ባላንበት ዘመን ከምንሰማቸው ነገሮች ጋራ ለማነጻጸር ሞክር።
7. "...ላመኑበት ጌታ አደራ ሰጧቸው" ቁ23 "...ለእግዚኣብሄር ጸጋ አደራ ወደ ተሰጡበት..." ቁ 26 የእነዚህ ዓይነት አባባሎች ስለ አገልግሎት ወይም ስለ አገልጋይ ምን ያስተምርሃል?
8. "በደረሱም ጊዜ ቤተ ክርስትያኑን ሰብስበው... ተናገሩ።" ቁ 27 ይህንን ስታነብ እያንዳንዱ አገልጋይ ለቤተ ክርስትያን ሊኖረው ስለሚገባው ተጠያቂነት ምን ታያልህ? በትለይ ይህንን ያደረጉት ሰዎች ጳውሎስና በርናባስ መሆናቸውስ ምን ያሳይሃል?
9. በዛሬው ጥናት በህይወትህ ለማስገባትና ለመጠቀም የወሰንከው እውነት ካለ ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት አሥራ አምስት፥ (ሐዋ ሥራ 15፥1-41)

**የጥናቱ ዓላማ፥ አለመግባባት በቤተ ክርስትያን ሊከሰት የሚችል ነገር እንደሆነና አለመግባባትን በምን ዓይነት መፈታት እንደሚኖርብን ለመማር።**

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንዲህ የከረረ አለመግባባት በመካከላቸው ስለተፈጠረ እርስ በእርስ ተለያዩ፤ ስለዚህ በርናባስ ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ፡፡›› ሥራ 15፡39

1. የሐዋ ሥራ 15፥1-41 በአንድነት በማንበብ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካሄደውን ነገር በራስህ አማርኛ ለማስረዳት ሞክር?
2. “እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም።” የሚለው ሃሳብ በዘመናችን ብዙ በግልጽ ላንሰማው እንችላለን። ነገር ግን አማኞችን ሊከፋፍሉ የሚችሉ ሌሎች ምን ነገሮች ይኖራሉ ትላለህ?
3. ያለመግባባቱን ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም አምጥተው ለሐዋርያቱና ለሽማግሌዎቹ ማቅረባቸው ለእኛ እንደግለሰብም ሆነ እንደ ቤተክርስትያን የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
4. አለመግባባቱ የተፈጠረው በማንና በማን መካከል ነበረ? ያለመግባባቱስ ምክንያት ምን ነበረ?
5. ችግሩን ለመፍታት የተወሰዱት ቅደም ተከተሎች ምን ነበሩ? ከውይይቱስ መንፈስ ምን ታያለህ?
6. የውይይቱ ውጤት ምን ነበረ?
7. ለዘመናችን የሚጠቅሙ ምን ዓይነት መመሪያዎችን ከዚህ ውስጥ ታያለህ?
8. በራስህ ህይወት ከወገኖች ጋራ አለመግባባት ቢገጥምህ ልትጠቀምበት የምትችለው ከዚህ ጥናት ውስጥ ምን ትምህርት አገኘህበት? ከዛሬው ጥናት የተማርከውን ለወገኖች አካፈል።

# ጥናት አሥራ ስድስት፥ (ሐዋ ሥራ 16፥1-40)

የጥናቱ ዓላማ፡ እግዚአብሄር ለሚያዘን ነገር ወዲያው መታዘዛችን የሚያመጣውን በረከት እንዳለ ለመመልከት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጳውሎስ ይህንን ራዕይ ካየ በኂላ እግዚአብሄር ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ጠርቶናል ብለን በመወሰን ወዲያው ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ፈለግን፡፡›› ሥራ 16፡10

1. ሐዋ ሥራ 16፥1-10ን በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ በምን አይነት መንገድ ነበረ የሚሄድበት አቅጣጫ የተነገረው?
2. ከዚህ ክፍል ምሪትን በተመለከተ የምናያቸው እውነቶች ምንድናቸው?
3. ሐዋ ሥራ 16፥11-40 ስናነብ ጳውሎስ ለእግዚአብሄር ጥሪ ወዲያው ምላሽ ሲሰጥ እናያለን። መቄዶንያ ሲደርስ የመታዘዙ ትክክለኛነት የተረጋገጠው በምን መንገድ ነበረ?
4. ሰዎች የወንጌልን እውነት ለመታዘዝ እንቢ የሚሉባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። በቁ 16-21 ለምናያቸው ሰዎች ገንዘብ ምክንያታቸው ሆኖ ይታያል። ዛሬስ ሰዎች እውነትን ላለመቀበል ምክንያት ሲሆናቸው የምታያቸው ነገሮች ምንድናቸው?
5. በቁ 30 ላይ የወህኒው ጠባቂ "እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል" የሚለውን ጥያቄ እንዲጠይቅ የእግዚአብሄር ባሪያዎች የተጫወቱት ሚና ምን ነበረ ትላለህ?
6. በጳውሎስ መታዘዝ ምክንያት መንፈሳዊ በረከት የደረሳቸው ቢያንስ ሶስት ግለሰቦችን ዘርዝር።
7. ወደ መቄዶንያ የጠራውን የእግዚአብሄርን ድምጽና ጥሪ ለመታዘዝ ጳውሎስ እንቢ ቢል እንደሰው አስተሳሰብ ምን ሊያስከትል የሚችል ይመስልሃል?
8. እኛም በግል ህይወታችን እንድናደርገው ወይም ደግሞ እንድንተወው ቃሉ የሚነግረን ነገር እለት በእለት ይኖራል። ብንታዘዝ ለራሳችንና ለሌሎችም በረከት እንሆናለን። እግዚአብሄር በቃሉ ሲናገርህ ለመስማት ምን ያህል ጆሮህ የተከፈተ ነው? የሰማኸውንስ ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት አሥራ ሰባት፥ (ሐዋ ሥራ 17፥1-34)

የጥናቱ ዓላማ፥ የምናገለግላቸውን ሰዎች አይነትና ባህላቸውን መረዳት የወንጌልን እውነት በሚገባቸውና በሚረዱት መንገድ ለማስተላለፍ እንደሚጠቅም ለማሳየት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ይዘውም አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ሥፍራ በመውሰድ እንዲህ አሉት፤ አንተ የምታስተምረው ይህ አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እንድናውቅ ትፈቅዳለህን?›› ሥራ 17፡19

1. ሐዋ ሥራ 17፥1-34 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው በሶስት ከተሞች ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌልን ሲናገር እናያለን። በተሰሎንቄና በቤርያ የነበረውን አገልግሎት አነፃፅር።(አቀራረቡን፥ሰዎች አቀባበላቸውን፥ውጤቱን ወዘተ
2. ጳውሎስ በአቴና የነበረው አገልግሎት(16-34) ደግሞ በተሰሎንቄና በቤርያ ከነበረው አገልግሎት(1-15) ጋራ በማነጻጸር ተናገር።
3. በአቴና የነበሩት ሰዎች ለጳውሎስ ትምህርት የሰጡት ምላሽ ምን ነበረ?
4. ለመልዕክቱ መነሻ በማድረግ ሐዋርያው የተጠቀመበት በመሰዊያው ላይ የተቀረጸው “ለማይታወቅ አምላክ” የሚለውን ጽሁፍ ነበረ። ዛሬስ የወንጌል ውይይት ለመክፈቻ የሚረዱ ምን ነገሮች ወደ አዕምሮህ ይመጣሉ?
5. ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች ልክ ለተሰሎንቄና ለቤርያ ሰዎች የወንጌልን እውነት አለባቅረቡ የሚያሳይህ ነገር ምንድነው? አቀራረባችንን ልንቀይርላቸው የምንችለው ሰዎች አይነት እስቲ ምሳሌዎችን በመስጠት አስረዳ።
6. ጳውሎስ አቀራረቡ ይለያይ እንጂ በነጥቦቹ ተመሳሳይነትን እንመለከታለን። እነዚህን ነጥቦች ለይተህ ተናገር።(ቁ 3, 18, 24-28, 30-31)
7. አቀራረብን የተለየ ማድረግ መልዕክትን ከመበረዝ በምን ትለየዋለህ? ይህ ሊከሰት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በምሳሌ አቅርብ።
8. ወንጌልን ሰዎቹ ባሉበት ሁኔታና የባህል አይነት ማቅረብ ቅድመ ዝግጅት ታደርጋለህ ወይ?

# ጥናት አሥራ ስምንት፣ (ሐዋ ሥራ 18፥1-28)

የጥናቱ ዓላማ፣ እግዚአብሄርን ለማገልገል በምናደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ ከሌሎች ወገኖች ጋራ የሚኖሩን ግንኙነቶች ምን ያህል ትልቅ ስፍራ ልንሰጣቸው እንደሚገባን ለመመልከት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በፈለገ ጊዜ ወንድሞች አበረታቱት፤ በዚያ የነበሩት ደቀ መዛሙርትም እንዲቀበሉት ደብዳቤ ጻፉለት፡፡›› ሥራ 18:27

1. ሐዋ ሥራ 18፥1-28 በማንበብ በጳውሎስ ህይወት ውስጥ የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር።
2. ጳውሎስ ከጵርስቅላና ከአቂላ ጋራ የነበረው ግንኙነት ጠቃሚ የሚያደርገው ነገር ምን ይመስልሃል?(2-4, 18-19)
3. ሲላስና ጢሞቲዎስ በሐዋርያው ጳውሎስ ህይወትና አገልግሎት ውስጥ የነበራቸው አስተዋጽዖ ምን ነበረ?
4. በህይወትህና በአገልግሎትህ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሰዎች አሉህ ወይ? አንተስ ምን ያህል በሰዎች ህይወትና አገልግሎት ውስጥ አስተዋጽዖ ለማድረግ ትተጋለህ?
5. ለምን ይመስልሃል እግዚ አብሄር በቁጥር 9-11 ላይ ለባሪያው የማጽናናትና የማበረታቻ ቃል መስጠት ያስፈለገው? በዚያች ከተማ አመት ከስድስት ወር ቆይቶ ማስተማሩ የሚያሳየን ነገር ምንድነው
6. ቁጥር 18-23 ትን በማንበብ ስለ ጳውሎስ ግንኙነቶች የምትማረው ነገር ምንድነው?
7. አጵሎስን በአጭሩ ለመግለጽ ሞክር(24-26)። ስለዚህ ሰው ይህንን ሁሉ ማለት ከተቻለ አቂላና ጵርስቅላ ሊሰጡት ያስፈለገው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
8. ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር የነበረው ግንኙነት ለአጵሎስ አገልግሎት አስተዋጽዖ ሲያደርግ የምታየው እንዴት ነው (ቁ 27-28)
9. እነዚህን ግንኙነቶች በማየት ያሉህን ግንኙነቶች ስለመንከባከብና ስለመገንባት ምን ተማርክ? ስላሉአችሁ ግንኙነቶች እግዚአብሄርን ማመስገን አትርሱ።

# ጥናት አሥራ ዘጠኝ፣ (ሐዋ ሥራ 19፥1-20፥12)

**የጥናቱ ዓላማ፣ እግዚአብሄር ድንቅና ተአምራቶች ለወንጌል መስፋፋት መንገድ አድርጎ የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች እንደሆኑ ለመመልከት።**

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ካመኑትም ሰዎች ብዙዎች እየቀረቡ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ ተናዘዙ፤ ሲጠነቁሉም ከነበሩት መካከል ብዙዎች መጽሐፋቸውን ሰብስበው በማምጣት በህዝብ ፊት አቃጠሉ፡፡›› ሥራ 19:19

1. ሐዋ ሥራ 19:1-20:12 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ምዕራፍ 19፡1-41 ትን በማንበብ እግዚአብሄር ሃይሉን የተገለጠባቸውን ሁኔታዎች ተናገር።
2. ወንጌል በግልጽ ሲሰበክ ሁልጊዜ የሰዎች አቀባበል ይለያያል። በዚህ ክፍል ሰዎች ለወንጌል ስብከቱ የሰጡትን የተለያዩ ምላሾች ምን ምን ዓይነት እንደነበሩ ተናገር።
3. በምዕ 19፥1-10 ባለው ክፍል ጳውሎስ ሰዎችን በእግዚአብሄር ቃል ለማሳደግ (ለማስተማር) የተጠቀመባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር።
4. "አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው ...ከእነርሱ ርቆ ደቀመዛሙርትን ለየ፤" የዚህ አይነቱ የጳውሎስ አሰራር ለእኛስ የሚያስተምረን ነገር አለወይ?
5. በ19፥11-20 የተካሄዱትን ነገሮች በራስህ አማርኛ ለመናገር ሞክር።
6. በ19፥11-12 በጳውሎስ ሕይወት የተከናወኑት ነገሮች አሁንስ በዘመናችን ሊከናወኑ ይችሉ ይመስልሃል ወይ? መሃረብና ጨርቅ የመሳሰሉ ነገሮችን ለፈውስ የሚልኩ ሰባኪዎች እንዳሉ ይታወቃል፤ ይህንን በተመለከተ ሃሳብ ተለዋወጡ።
7. 19፥20 "እንዲህም የጌታ ቃል በሃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።" በዚህ ክፍል መሰረት ለእግዚአብሄር ቃል እድገትና ማሸነፍ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው ትላለህ?
8. እግዚአብሄር ድንቅና ተአምር ሲደርግ ገጥሞህ ያውቃል ወይ? ጌታ በውስጣችን ከሰራው ተዓምራት ሌላ በሰዎች አካልም ላይ ተአምር አድርጎ ለወንጌል ማስፊያ ሊጠቀምበት ይችላል፤ ሆኖም ክብሩ ሁሉ ለርሱ ይሁን፡፡

# <u>ጥናት ሃያ (ሐዋ ሥራ 20፥13-38)</u>

የጥናቱ ዓላማ፡ የክርስቶስ ወንጌል አገልጋይ የሆነ ሰው ትምህርትን ተግሳጽን ፥ምክርን እንዲሁም እርማትንም በመጠቀም ሚዛን በጠበቀ ሁኔታ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የእግዚአብሄርን ፈቃድ ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽ የተቆጠብኩበት ጊዜ የለምና።›› ሐዋ ሥራ 20:27

1. ሐዋርያት ሥራ 20፥13-38 በአንድነት ይነበብ። ይህን ክፍል ሲነበብ የተሰማህ ስሜት ምንድነው?
2. ጳውሎስ በ20፥18-21, 26-27, 31, 33-35 በኤፌሶን ስለነበረው አገልግሎቱ የሚላቸውን ነገሮች ዘርዝር።
3. ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ከተናገራቸው ነገሮች መሃል በህይወትህ መጨረሻ ልትላቸው የምትወዳቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
4. "የእግዚአብሄርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና፤" የሚለው አባባል የወንጌል አገልጋይ በሃላፊነት ለተሰጠው መንጋ ማስተማር ስለሚኖርበት ነገር ምን ያስተምርሃል?
5. ጳውሎስ በህይወቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው (ቁ 22-25)? በአንተ ህይወት ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ነገሮች ከእርሱ ጋራ በማነጻጸር ተናገር።
6. 20፥28-31 ላይ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የሰጣቸውን መመሪያዎች ዘርዝር።
7. ጳውሎስ በቁ 32 መሰረት እነዚህን ሽማግሌዎች በሙሉ ልብ ሳያወላውል ትቶአቸው ለመሄድ የደፈረበት ምክንያት ምን ነበረ?
8. በዚህ ክፍል መሰረት ጳውሎስ ለእነዚህ እረኞች የህይወቴን ምሳሌነት ተከተሉ የሚላቸው ይመስልሃል ወይ? ይህንን የምታየው ከየትኞቹ ክፍል ውስጥ ነው?
9. ቁ 36-38 የምታያቸውን ቢያንስ አምስት የፍቅር መግለጫዎችን ዘርዝር። ካለህበት ወገኖች የምትለይበት ጊዜ ቢመጣ እንደነዚህ ባሉ በፍቅር መግለጫዎች የተሞላ የሚሆን ይመስልሃል ወይ?

# ጥናት ሃያ አንድ (ሐዋ ሥራ 21፡1-40)

**የጥናቱ ዓላማ፣** ህይወታችንን ለሞተልን ጌታ ለመኖርና ለእርሱ ለመሞት ከቆረጥን ማናቸውም ዓይነት አስፈሪ ሁኔታ ቢገጥመን ሊበግረን እንደማይችል ለመመልከት፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለምን እንዲህ እያለቀሳችሁ ልቤን ታባቡታላችሁ? እኔ መታሰር ቀርቶ ስለጌታ የሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ዝግጁ ነኝ አላቸው፡፡›› ሥራ 21፡13

1. **ሐዋ ሥራ 21፥1-26 በአንድነት ይነበብ። በቁ4 ና 10-12 ባለው ክፍል የሆነውን ነገር በአጭር አነጋገር ገለጠው፡፡**
2. በቁ8-10 ላይ ተጠቅሰው የምናገኛቸው የጸጋ ስጦታዎች የትኞቹ ናቸው? በተለይ የትንቢት ስጦታው ያካተታቸውን ሰዎች ስናይ ልንደርስበት የምንችለው ውሳኔ ምንድነው?
3. **ጳውሎስ ለተነገሩት ማስጠንቀቂያዎች የሰጠውን ምላሽ ምን ነበረ?**
4. በቁ12-14 በሰፈረው መሰረት ስለ ጳውሎስ በተነገረው ትንቢት ላይ በጳውሎስና በሌሎቹ ወገኖች መሃል የነበረው የአስተሳሰብ ልዩነት ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ፡፡ ልዩነታቸውን የፈቱት በምን መንገድ ነበረ?
5. ጳውሎስ የነብያቱን ትንቢት እየሰማ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ ትክክል ነው ብለህ ትገምታለህ ወይ? ለምን? ሰፋ አድርጋችሁ ተወያዩበት፡፡
6. **ቁጥር 17-26 ያለውን ክፍል ስታነብ በጳውሎስና በሐዋርያት እንዲሁም በሽማግሌዎች መሃል ስለነበረው ግንኙነት ምን ትረዳለህ?**
7. በቁ27-40 ውስጥ የተከናወነውን ነገር በአጭሩ ተናገር፡፡ ይህ የተከሰተው ሁኔታ ስለ ቀደም ብለው ስለተናገሩት ነብያት ምን ይነግርሃል?
8. የጳውሎስ ወሳኔ ምን ያስተምርሃል? ኢየሱስን ማመንህ ዋጋ አስከፍሎህ ያውቃል ወይ? ስለ ኢየሱስ ምን ያህል ዋጋ ልትከፍል ተዘጋጅተሃል?

# <u>ጥናት ሃያ ሁለት (ሐዋ ሥራ 22፡1-30)</u>

**የጥናቱ ዓላማ፥** ለጌታ ለመሞትም እንኳን መቁረጥ ማለት በሞኝነት እግዚአብሄር ያዘጋጀልንን የደህንነት በር መዝጋትና ለማይገባ አደጋ ራስን ማጋለጥ ማለት እንዳልሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ጳውሎስም በጠፍር ወጥረው ሲገርፉት ሲሉ፤ አጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ፤ አንድን የሮም ዜጋ ያለፍርድ ለመግረፍ ህግ ይፈቅድላችኋልን? አለው።
ሐዋ ሥራ 22፡25

1. የሐዋ ሥራ 22፡1-30 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-5 ላይ ጳውሎስ ስለራሱ የሚናገራቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝሯቸው። ለምንድነው ይህንን ሁሉ መዘርዘር ያስፈለገው?
2. በቁ6-21 ላይ የሚተርከው ነገር ምንድነው? ይህ ለሰዎቹ የነገረው ነገር በሐዋ ሥራ 9 ውስጥ ከሰፈረው ታሪክ ጋራ ስታስተያየው ምን ያህል ተመሳሳይነት ታይበታለህ?
3. ‹‹ሕዝቡም ይህንን ቃል እስኪናገር ድረስ ሰሙት፤›› የሚለው የትኛውን ቃል ሲያመለክት ነው?ይህ የተባው ቃልስ እነዚህን ሰዎች ይህንን ያህል ያስቆጣበት ምክንያት ምንድነው?
4. በቁ22-29 ባለው ክፍል የተካሄደውን ሁኔታ በአጭሩ እንዲገልጹ ለሁለት ሰዎች ዕድል ይሰጥ።
5. ጳውሎስ ለምንድነው በዚህ ክፍል ሮማዊነቱን መግለጥ የፈለገው ብለህ ትገምታለህ? ይህንንስ ማድረጉ ሊደርስበት ከነበረው መከራ እንዲድን ምን ያህል አስተዋጽዖ አድርጎለታል ብለህ ታምናለህ?
6. ይህ የተጠቀመው ታክቲክ ሊደርስበት ከነበረው መከራ ያስመለጠው ከሆነ፤ በሐዋ ሥራ 21፡13 ለጌታ ‹‹ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነኝ›› ካለው አባባሉ ጋራ እንዴት ሊታረቅ እንደሚችል አስረዳ።
9. ጥበብ ብለው ውሸትን የሚጠቀሙ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ? አንተስ ከአንድ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት ጥበብ ተጠቅመህ ታውቃለህ ወይ? ጥበብንና ውሸትን ለመለየት ጌታ ጥበብ እንዲሰጣችሁ ለምኑ??

# <u>ጥናት ሃያ ሶስት (ሐዋ ሥራ 23፡1-35)</u>

***የጥናቱ ዓላማ፣ ለእግዚአብሄር ነገር ከጨከንና ራሳችንን ከሰጠን እግዚአብሄር ደግሞ የሚሰነዘርብንን ሴራ እንደሚያከሽፍና ከንቱ እንደሚያደርግ ለመማር።***

*የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ፤ ጳውሎስ ሆይ፤ አይዞህ! በኢየሩሳሌም እንደመሰከርክለኝ በሮምም ደግሞ ስትመሰክርልኝ ይገባል፡፡›› ሥራ 23፡11*

1. የሐዋ ሥራ 23፡1-35 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምዕራፍ መክፈቻ ላያ ጳውሎስ ተከሶ የቀረበ በማን ፊት ነው? ቁ1-5 ውስጥ የተካሄደው ድራማ በራስህ ቋንቋ ግለጽ፡፡
2. ጳውሎስ በምዕ 22፡25-27 ላይ የተጠቀመውን ዓይነት በ23፡6-10 ላይም ሲጠቀም እናያለን፡፡ ይህ አይነቱ መንገድ እንደ ሥጋዊ አሰራር ወይስ ከእግዚአብሄር እንደተሰጠ ጥበብ ታየዋለህ? ለምን?
3. በተለያዩ ነብያት ኢየሩሳሌም ከሄደ መከራ እንደሚገጥመው ተነግሮት ዝምብሎ መሄዱ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንደጣሰ ተደርጎ ይነገራል።ይህንን በተመለከተ የአንተስ ሃሳብ ምንድነው? 23፥11 ከዚህ አመለካከት ጋራ ይጣጣማል ወይ?
4. በ23፥6-10 በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል መለያየትን የተፈጠረበት ምክንያት ምን ነበረ?
5. 23፥12-22 ስታነብ እግዚአብሄር ጳውሎስን ለማዳን የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበረ?
6. በዚህ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር ጳውሎስን ለመታደግ የተጠቀመባቸው መንገዶች ብለህ የምታምናቸውን ሁሉ ተናገር፡፡ እግዚአብሄር ጳውሎስን ለማዳን ያደረገውን ስታይ ለአንተ ምን ትምህርት ያስተምርሃል?
7. ሐዋ ሥራ 19፥21ን ስናነብ ጳውሎስ ወንጌልን በሮም ለመስበክ እቅድ እንዳለው ይታያል። በ23፥23-24 ደግሞ ወደ ሮም የመሄጃውን ጅማሬ በእግር ጉዞ ሳይሆን በብዙ አጀብና በፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲላክ ይታያል። ይህንን ስታይ ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን ትማራለህ።
8. ከዚህ ክፍል ውስጥ ለግል ህይወትህ የተማርከውና ማካፈል የምትወደው ነገር ካል አካፍል።

# ጥናት ሃያ አራት (የሐዋ ሥራ 24፡1-27)

**የጥናቱ ዓላማ፡ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ አማኝ የወንጌልን እውነት ሊያስተላልፍ እንደሚችልና በመልዕክቱ ቅድሚያ መስጠት የሚኖርበትን ማወቅ እንዲችል ለመማር፡፡**

**የጥናት መክፈቻ፡** ‹‹ጳውሎስን ስለ ጽድቅና፤ ራስን መግዛት፤ ስለሚመጣውም ፍርድ በሚናገርበት ጊዜ…›› ሥራ 24፡25

1. የሐዋ ሥራ 24፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ 5-9 ባለት ቁጥሮች ስትመለከት፤ **ጳውሎስ የተከሰሰበት ክስ ምን እንደነበረ አስረዳ።**
2. **24፥2-4 ፊሊክስን የሚያሞካሹበትን ማሞካሸት ስታይ ስለ ከሳሾቹ ምን ይነግርሃል?**
3. **በ24፥10-21 ጳውሎስ ያቀረበውን የመከላከያ ንግግር ይዘት እንዴት ታየዋለህ?**
4. **በም 24፥14-16 ውስጥ ስታነብ ጳውሎስ እግዚአብሄርን አመልካለሁ በማለት የሚጠቅሳቸውን ነገሮች ዘርዝር። እነዚህ ነገሮች ለአንተስ ምን ያህል ወሳኝነት ያላቸው ነገሮች ሆነው ታያቸዋለህ?**
5. **24፥24 ፊሊክስ ስለክርስቶስ ለመስማት ጳውሎስን እንዳስጠራው እናያለን። ይህንን ለማድረግ የገፋፋው ከጳውሎስ ድርጊት ምኑ ይመስልሃል? (24፥10-16)**
6. **ፊሊክስ ስለ ክርስቶስ እንዲያሰማው ሲጠራው ጳውሎስ ያተኮረባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?**
7. **ለምን ይመስልሃል ጳውሎስ በእነዚህ ሶስት ነገሮች ላይ ብቻ ሊያተኩር የፈለገው? ከእነዚህ ከሶስቱ ፊሊክስን እንዲፈራ ያደረገው የትኛው የትኛው ሃሳብ ነው ብለህ ታስባህ?**
8. **ወንጌልን ስትናገር በምን ላይ ትኩረት ታደርጋለህ? ከዚህ ክፍል ስለ ወንጌል መልዕ ክት አቀራረብ ምን የምትማረው ነገር አለ?**

# ጥናት ሃያ አምስት (ሐዋ ሥራ 25፡1-27)

የጥናቱ ዓላማ፡ እንደጳውሎስ እኛም እግዚአብሄር በከፈተልን ዕድል ሁሉ የሞተውንና ከሙታን ድል አድርጎ የተነሳውን ኢየሱስን እንድንናገር ለማበረታታት፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሞቶ ስለነበረው፤ ጳውሎስ ግን ሕያው ነው ስለሚለው ሰው፤ ስለ ኢየሱስ ይከራከሩ ነበር፡፡›› ሐዋ ሥራ 25፡19

1. የሐ ሥራ 25፡1-27 ይነበብ፡፡ በቁ1-5 ላይ የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች ጥያቄ ምን ነበረ? እግዚአብሄር በምን መንገድ ለባሪያው ተከላከለ?
2. ቁ6-7ትን ስናነብ አይሁድ ሰላቀረቡት ክስ ምን እንረዳለን? የጳውሎስስ መልስ ምን ነበረ? ከጳውሎስ አነጋገር ምን ዓይነት ስሜት ታስተውላለህ?
3. በቁ13-21 ድረስ በፊስጦስና በንጉሥ አግሪጳ መሃል የሚደረገውን ውይይት በአጭሩ ተናገር፡፡
4. ከላይ በተመለከትነው ክፍል ውስጥ ፊስጦስ በጳውሎስ ላይ የሚያደርገውን ነገር ወስኖ ሳለ ለምንድነው ከንጉስ አግሪጳ ጋራ መወያየት የፈለገው?
5. በቁ16-19 ላይ ፊስጦስ ስለክርስትና እምነት ዋነኛ አድርጎ የሚጠቅሰውና ጳውሎስ ከተናገረው ውስጥ ያስታወሰው እውነት ምን ነበረ?
6. ከአንተ ምስክርነት ውስጥስ ሰዎች በአዕምሮአቸው የሚቀርና ተመልሰው ሊያስታውሱት የምትፈልገው እውነት ምንድነው?
7. ንጉስ አግሪጳ ከጳውሎስ ሊሰማ የፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ሐዋ ሥራ 25፥22
8. እግዚአብሄር በሚሰጥህ ዕድል የየሱስን መሞትና መነሳት ለመናገር ምን ያህል ትጠቀማለህ? ዛሬ ከተማርከው የቀረልህን ተናገር፡፡

# ጥናት ሃያ ስድስት (ሐዋ ሥራ 26፡1-32)

የጥናቱ ዓላማ፡ ሰዎች ንስሃ ገብተው በይቅርታ ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ ብቻ ሳይሆን ሌላውን አቅጣጫ ማለትም የንስሃ ፍሬ ማፍራት እንደሚጠበቅባቸውም መናገር ሃላፊነታችን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚያም ለአህዛብ ንስሃ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ፤ የንስሀም ፍሬ እንዲያሳዩ ገልጬ ተናገርሁ፡፡›› ሐዋ ሥራ 26፡20

1. ሐዋ ሥራ 26፡1-32 ይነበብ፡፡ ምዕራፉ ያተኮረው በጳውሎስ መከላከያ ላይ ስለሆነ መከላከያ አድርጎ ያቀረባቸው ሃሳቦች ምን እንደነበሩ ተወያዩባቸው፡፡
2. ከቁ9-18 ባለው የጳውሎስ የደህንነት ታሪክ የሚናገር ነው፡፡ ይህንን እርሱ በህይወቱ ያለፈውን ነገር መስማቱ ለንጉሥ አግሪጳ ምን ይጠቅመዋል?
3. ቁ16ትን ስናነብ ኢየሱስ ጳውሎስን ለሁለት ነገሮች ምስክር እንዲሆነው ሾሞታል፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በሁለቱ ሃሳቦች ምንነት ላይ ተነጋገሩባቸው፡፡
4. ንጉስ አግሪጳ እንዲድን ጳውሎስ ትልቅ ፍላጎት እንደነገረው የሚጠቁሙንን ጥቅሶች ከምንባቡ ውስጥ አሳይ፡፡ ለፍርድ ቀርቦ እያለ ከራሱ መፈታት ይልቅ ለሚፈርድበት ሰው ደህንነት መጨነቁ ስለዚህ ሰው ምን ያስተምረናል?
5. ቁ17-18 እግዚአብሄር አደርጋለሁ ያላቸውን፤ ጳውሎስን ታደርጋለህ ያላቸውንና በሰዎቹ ህይወት ውስጥ ደግሞ ይከናወናል ያላቸውን አንድ በአንድ ዘርዝሩ፡፡ ይህ ዓይነቱ ተልዕኮ ለጳውሎስ ብቻ ነው ወይስ እኛንም ይመለከታል?
6. ቁ19-20 ላይ የምናየውን የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ቅደም ተከተል በሐዋ ሥራ 1፡8 ላይ ኢየሱስ ለሐዋርያቱ ከሰጠው ቅደም ተከተል ጋራ በማነጻጸር ተነጋገሩባቸው፡፡
7. በቁ20 ላይ ጳውሎስ ለአህዛብ ወንጌልን ሲሰብክ ያተኮረባቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ይህንንስ ስለተናገረበት መንገድ ከክፍሉ ምን እናያለን?
8. ሰዎች ጌታን ከመቀበል ሌላ የንስሃን ፍሬ እንዲያሳዩ በተጨማሪ ትነገራህ ወይ? ንስሃ የገባ የንስሃ ፍሬ ማፍራት ስላለበት ያንንም መንገር ተገቢ ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ሰባት (ሐዋ ሥራ 27፥1-44)

የጥናቱ ዓላማ፡- በአስጨናቂና በሚያስፈራ ሁኔታ መሃል እንኳን አማኝ ልቡን በእግዚአብሄር ላይ አሳርፎ ሊኖር እንደሚገባው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አሁንም ቢሆን አይዟችሁ! መርከቧ እንጂ ከእናንተ አንዲት ነፍስ እንኳ አትጠፋምና።›› ሐዋ ሥራ 27:22

1. ሐዋ ሥራ ምዕ 27፥1-44 በአንድነት ይነበብ። በእነዚህ ምዕራፎች ጳውሎስን በእስር ሆኖ ወደ ሮም ሲወሰድ እናያለን። በነፃነት ሳለና አሁን የሚሰራቸውን ታስሮ ሳለ የሚያደርጋቸው ነገሮች ልዩነት ታያለህ ወይ? ይህ ምን ያስተምርሃል?
2. ቁ 27፥3 ዩልዮስ ጓደኞቹን እንዲያይ መፍቀዱ ስለ ጳውሎስ ምን የሚነግርህ ነገር አለ?
3. ከተነበበው ምንባብ ውስጥ ጳውሎስ በእግዚአብሄር ላይ ስላለው መደገፍና የልብ ሙላት የሚያሳየን የትኛው ክፍል ነው?
4. 27፥33-38 ጳውሎስ በአምላኩ ላይ የነበረው ልበ ሙሉነት ለሌሎች የተረፈ ይመስልሃል ወይ? አብራራ።
5. 27፥7,8,16 "በጭንቅ" የሚለው ሃሳብ ሲደጋገም እናያለን። ያመነም ያላመነም በተመሳሳይ ነገር ውስጥ ሲያልፉ እናያለን። ታዲያ በዚህ መሃል በጳውሎስና በሌሎቹ መካከል ሁኔታውን የተቀበሉበትን የአቀባበል ልዩነት ተናገር።
6. "ጳውሎስ ሆይ አትፍራ በቄሳር ፊት ልትቆም ይገባሃል.." 27፥25 የሚለው ተፈጻሚ የሆነ ይመስልሃል ወይ? ከሆነስ ስለ እግዚአብሄር የተስፋ ቃል ምን እንማራለን?
7. "..ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋምና።" 27፥22 "እነዚህ በመርከቡ ካልቆዩ እናንተ ትድኑ ዘንድ አትችሉም አላቸው።" 27፥31 እነዚህ ሁለት ሃሳቦችን እንዴት ታስታርቃቸዋለህ?
8. ጭንቅ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ራስህን ስታገኝ ተረጋግተህ ሰውን ታረጋጋለህ ወይስ ተጨንቀህ ታስጨንቃለህ? ለሰዎች በክርስቶስ እረፉ የሚል ሰው በእርሱ ማረፍ ምን እንደሆነም በምሳሌነት ሊያሳይ ይገባዋል። በጌታ ማረፍን በተመለከተ የተማርከውን ነገር ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት ሃያ ስምንት (ሐዋ ሥራ 28፥1-31)

የጥናቱ ዓላማ፡- እንደ ጳውሎስ በጊዜውም ያለጊዜውም፣ በውጭም በእስር ቤትም የእግዚአብሄርን መንግሥት የመናገር ድፍረትና ጽናት እንዲኖረን ለማበረታታት፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ወደ ማረፊያ ስፍራው መጡ፤ እርሱም ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ስለ እግዚአብሄር መንግስት እየመሰከረ ያብራራላቸው ነበር፡፡›› ሐዋ ሥራ 28፡23

1. በ28፥1-6 ውስጥ በሚገኘው ክፍል በመላጥያ ደሴት ላይ ስለሚኖሩት አረማውያን ባህርይ የሚታዩትን ነገሮች ዘርዝር።
2. "ጳውሎስ ግን ብዙ ጭራሮ አከማችቶ.." ጳውሎስ በብዙ መንገድ በእስረኞቹ ብቻ ሳይሆን ወታደሮቹም እንደሚያከብሩት ይታያል። ታዲያ ይህ የጳውሎስ በሥራው እኩል ትካፋይ መሆን ስለ እርሱ ባህርይ ምን ይነግረናል?
3. በ28፥7 ላይ ፑፕልዩስ እንግዶቹን በፍቅር በመቀበሉ በደሴቲቱ ያስከተለው ነገር ምን ነበረ?
4. 28፥14 እነጳውሎስ እንዲያሳርፏቸው መለመን ሲገባቸው በተቃራኒ ቅዱሳንን ለማሳረፍ መለመናቸው ምን ያስተምርሃል? በዚህ ክፍልና በ2ኛ ቆሮ 8፥4 ምን ተመሳሳይነት ታያለህ?
5. ቁ 28፥15 ትን በማንበብ በዚያን ወቅት በአማኞች መሃል ስለነበረው ግንኙነትና ህብረት ምን የምንገነዘበው ነገር ይኖራል? በዘመናችን ከሚታየው ሁኔታ ጋራ በማነጻጸር ተናገር።
6. በሶስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት ወንድሞች ለነጳውሎስ ምንም ያደረጉት ነገር እንዳለ አናይም፥ ነገር ግን ጳውሎስ እግዚ አብሄርን እንዳመሰገነና ልቡ እንደተጽናና ይናገራል። ይህ የሆነው ለምን ይመስልሃል?
7. 28፥23, 31 ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ህይወት ለአንድ ነገር ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ እንደሆነ ቃሉ ሳይሆን ስራው ይመሰክራል። ይህ አንድ ነገር ምን ነበረ?
8. ሐዋ ሥራ 9፡20 እና 28፡31 የጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስበክ ጀምሮ እንደጨረሰ እንመለከታለን፡፡ አንተስ በእግዚአብሄር ነገር ጀምረህ በእግዚአብሄር ነገር ለመጨረስ ምን ያህል የህይወትህ ውሳኔ ነው?